# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2018 የነበረው

# የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፈዉ የኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ እና የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሸለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በዚሁ መሰረት በብዙ ቦታዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ ሰሜን አጋማሽ የሀገራችን አካባቢዎች በነዚህ ሁለቱ አስር ቀናት ዉስጥ በአብዛኛዉ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ነበር ተስተዋለዉ፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከነበረዉ ደመና በሰሜን፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በሌላ በኩል በወሩ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ላይ ወደ ሀገራች እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ላልጠበቀ ዝናብ እንዲኖር መንስዔ ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች ላይም ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይም ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ የምዕራብ ኦሮሚያ፣ ምስራቅ አማራ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ትግራይ፣ የደቡብ ህዝቦች እና ምስራቅ አካባቢዎች ላይም ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በሞያሌ 41.6፣ በባሌ ሮቤ 42.3፣ በአሶሳ 59.4፣ በሲርበ አባያ 40.2፣ በአሰበ ተፈሪ 47.5፣ በገዋኔ 46.6፣ በማጂ 30.2፣ በሀረር 39.1፣ በአብኣላ 30.1፣ በደብረታቦር 32.0፣ በጂንካ 39.7 እና 32.1፣ በሊሙገነት 34.1፣ በማጨዉ 37.5፣ በማንኩሽ 91.2፣ በሚሌ 52.4፣ በማፀምሪ 34.8፣ በሳዉላ 31.0፣ በቋራ 46.8፣ በአዲስ አበባ 38.8፣ በቡርጂ 74.4፣ በአምቦ 36.1 እና 32.1፣ በጨፋ 30.2፣ በሆሳና 35.2፣ በጅማ 39.5፣ በኢጃጂ 45.4፣ በባቲ 30.7፣ በቻግኒ 30.8፣ በዲላ፣ 37.8፣ በእነዋሪ 45.4፣ በነቀምቴ 33.4፣ በበደሌ 34.3፣ በሻምቡ 41.9፣ በአቦቦ 36.1 እና 33.2፣ በአድዋ 58.4፣ በአርጆ 32.2 እና በአይራ 40.7 በሚሜ ይገኙበታል::


ባለፈዉ የኦክቶበር ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በቤንሻጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል እና በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በአርሲ እና በባሌ፣ በጉጂ እና ቦረና ዞኖች ላይ ከ50-275 ሚ.ሜ ከ7-10 ቀናት ያህል የዘነበ ሲሆን፤ በትግራይ ክልል ዞኖች፣ በሸበሌ፣ በፋፈን፣ በአፋር ክልል ዞን 03፣ 04፣ 05 እና 02 ላይም ከ25-49ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7) ።

ባለፈዉ የኦክቶበር ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በትግራይ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በአማራ ክልል ከጥቂት የዋግህምራ እና ሰሜን ጎንደር ዞኖች በስተቀር ሁሉም ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል በሲቲ፣ በፋፈን እና ኖጎብ ዞኖች፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በጉጂ እና ቦረና፣ በአርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ በቤንሻጉል-ጉሙዝ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በጋምቤላ፣ በወለጋ፣ በኢሉባቦር፣ በጅማ እና በሸዋ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 8) ።


ካርታ 6   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ8   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2018 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር ወር የነበረው እርጥበት በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ እንደነበረ የተተነተኑ የአግሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም በምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ የሰሜን ኪስ ቦታዎች ላይ የተሻለ እርጠበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች በጎ ጎን ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከከባቢ የአየር እርጥበት መጨመር ጋር ተያይዞ በመደበኛ ሁኔታ በወሩ ውስጥ ይስተዋል የነበረው ጠንከር ያለ ቅዝቃዜና የውርጭ መከሰት የቀነሰበት እንደነበረ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት ከማሳ ዝግጅት አንስቶ ዘር ለመዝራት የሚያስችል መልካም አጋጣሚ የፈጠረ ሲሆን፤ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎችም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖባቸው የነበረ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በተለይም ዕድገታቸውን ለጨረሱ የመኸር ሰብሎች እንዲደርቁ ዕድል የፈጠረና የሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ነበር (ካርታ 9)።


ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2018 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ



# ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2018 የነበረው የአየር ጠባይ
# በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ኢ.ኤ.አ 1-31 ኦክቶበር 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅና በሰሜን ምእራብ የአገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል$ በዚህ መሰረት ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች አብዛኛኛዉ አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው ባሮአኮቦ ጥቂት የታችኛው አዋሽ፣ የመካከለኛውና የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛው ስምጥሸለቆና የታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ናቸው$ ከእርጥበታማ እስከ በከፊል እርጥበታማ ያለውን የእርጥበት መጠን ያገኙ ተፋሰሶች የላይኛውና መካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ ጥቂት የላይኛው ስምጥሸለቆና ኦሞጊቤ፣ ጥቂት የላይኛው አባይ እና የላይኛው ተከዜ የተሰተዋለባቸው ናቸው$ በኦክቶበር ወር ከባድ ዝናብ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የተመዘገበ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በተፋሰሶች ላይ ለዉሃ ሀብት ግብአት በመሆን ጠቃሚ ገፅታ ነበረዉ (ካርታ 10)።

ካርታ 10 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከኖቨምበር 1-30/2018 የሚኖረው
# የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቨምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ከማመዘኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት የሚታይበት ሲሆን፤ ከዚህም ሌላ በተዳከመ ሁኔታ ቢሆንም እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ እየዘነበ ይቆያል።

በሚቀጥለው ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ እንደሚስተዋል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ደረቃማ የአየር ጠባይ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክሮ እንደሚቆይ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጨምር እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ በጥቂት ደጋማ ቦታዎችም ላይ ውርጭ ሊከሰት ይችላል።ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል።

በመሆኑም በሚቀጥለው ወር <u>በአብዛኛው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል። ከዚህም ሌላ ከኦሮሚያ ዞኖች ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረረጌ እንዲሁም የጉጂ እና የቦረና፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች፤ በሶማሌ ክልል የሚገኙት የደገሀቡር፣ የፊቅ፣ የቆራሂ፣ የአፍዴር፣ የጎዴ እና የሊበን ዞኖች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በአንጻሩ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።</u>

# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30/2018 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ
# በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኖቬምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፣ በአብዛኛው የመኸር ሰብሎች ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ የሚከናወንበት ወቅት ነው፡፡ በአንፃሩ የደቡብና ደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች መጠነኛ የሆነ

እርጥበት የሚያገኙበት ወር ነው፡፡ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከርና የውርጭ ክስተት ሊኖር እንደሚችል በትንበያው ተመልክቷል፡፡ ምንም እንኳን ደረቃማው የእርጠበት ሁኔተ የሰብል ስበሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባን በስፋት ለማከናወን መልካም አጋጣሚ ቢኖረውም፤ ከጠንካራ ቅዝቃዜና ከውርጭ ክስተት ጋር ተያይዞ እንዳንድ እድገታቸውን ያልጨረሱና በተለይም በአበባና በዘር ሙሌት ላይ ለሚገኙ ሰብሎችና የፍራፍሬ ተክሎች ጉዳት ሊያስክትል ስለሚችል አርሶ አደሮችም ሆኑ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ጥንቃቄና ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ምንም እንኳን በእድገት ላይ ለሚገኙ የበጋ ወቅት ሰብሎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት በጎ ጎን ቢኖረውም የደረሱና ያልተሰበሰቡ ሰብሎችን ሊጎዳ ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## <u>እ. ኤ. አ ከኖቬምበር 1-30/2018 የሚኖረው የአየር ጠባይ</u>
## <u>አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በኖቨምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝንበት ወቅት ሲሆን በሌላ በኩል በተዳከመ ሁኔታ ቢሆንም እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ በሀገሪቱ በሚገኙ ተፋሰሶች ላይ ዝናብ የሚያገኙበት ወር ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የገናሌ ዳዋ፣ ዋቢሸበሌ፣ መካከለኛውና የታችናው አባይና የስምጥ ሸለቆ፣ ደቡባዊው የአባይ ክፍል እንዲሁም ጥቂት የላኛው የባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃችን ያመለክታል፡፡ የተቀሩት የሀገሩተ ተፋሰሶች ደረቃማ ሁኔታ ዉሰጥ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ዝናብ በሚያገኙ ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው ማህበረስብና በውሃ እንቅስቃሴ ላይ የሚሰሩ ተጠቃሚዎቻችን በተቻለ መጠን የሚገኘውን ውሃ ባግባቡ በመያዝ ለሚያስፈልገው እንቅስቃሴ እንዲያውሉ ለመግለፅ እንወዳለን፡፡